እራስን በራስ ማርካት (Masturbation)

መግቢያ

የማስተርቤሽን ርዕሰ ጉዳይ በሁሉም በዓለማችን ክፍል ከሚነሱ አከራካሪ እና ይዜ ነው ተብሎ ድምዳሜ ያልተሰጠው ሀሳቦች አንዱ ነው። ከ18ኛው ክፍለዘመን አንስቶ አሁን እስካለንበት ብዙ አዋቂ የሚባሉ ሰዎች በመንፈሳዊውም አቅጣጫ እንዲሁም ከዛ በተለየ መንገድ ብዙ ዕሁፎችን ዕፈዋል። አሁንም ድረስ በተለያየ እይታ ብዙ ይባላል። በአብዛኛው ሀገራት በግልዕ (Public) ይህንን ተግባር ማድረግ በህግ አይፈቀድም።

እራስን በራስ ማርካት በብዙ ሰዎች ዘንድ መፍትሄ እስካልተገኘለት እንደ ልምምድ የሁል ጊዜ ተግባር ሆኖ የመቆየት አቅም ያለው ድርጊት ነው። ብዙዎች ለመላቀቅ እየፈለጉ እንኳን በቀላሉ ሊወጡበት እያቃታቸው እንዲሁም አንዳንዶች ተመችቷቸው በዛው ልምምድ ውስጥ ይኖራሉ።

እራስን በራስ ማርካት ምን ማት ነው?

እራስን በራስ ማርካት ማለት በተፈጥሮ ከሚታወቀው ማለትም በሁለት ሰዎች (ወንድ እና ሴት) መካከል በሚደረግ የግብረስጋ ግንኙነት ሊገኝ የሚችልን ወሲባዊ እርካታ (Orgasm) ለብቻ በመሆን ለማግኘት ሲባል የሚፈፀም ድርጊት ነው። ድርጊቱ በተለያየ መንገድ ይፈፀማል። <u>ለምሳሌ :-</u> በእጅ ፣ በጣት ፣ ለቀን ተዕለት በምንጠቀምባቸው ቁሳቁስ እንዲሁም ለዚህ አላማ በተዘጋጁ ቁሳቁስ በመጠቀም ሊተገበር ይችላል።

ስታትስቲክስ

እራስን በራስ ማርካት የዘወትር ልምምዳቸው ያደረጉ ሰዎች በፐርሰንት ምን ያህል እንደሆኑ STATSTIC BRAIN ከሚባል Website ያገኘሁት ጥናታዊ መረጃ እንዲህ ይለናል።

- በዚህ ልምምድ የተጠመዱ :- ወንዶች 95 % ሴቶች 89 %
- በየቀኑ የሚያደርጉ :- ወንዶች 40 % ሴቶች 22 %
- በሳምንት አንድ ጊዜ የሚያደርጉ :- ወንዶች 55 % ሴቶች 48
- ያገቡ :- ወንዶች 70 % ሴቶች 70 %
- የተለያዩ ቁሳቁስ የሚጠቀሙ :- ወንዶች 17 % ሴቶች 53 %
- ወደዚህ ልምምድ በድንገት የገቡ ከሁለቱም ፆታ 41 % ሲሆኑ ሆን ብለው የጀመሩ ደግሞ 22.6 % ያህል ናቸው። [#በድንገት የገቡ የተባሉት ጓደኞቻቸውን በማየት / ካለማወቅ / ከፖርኖግራፊክ ቪዲዮዎች በመመልከት... የመሳሰሉት ሲሆን #ሆን ብለው የጀመሩት ደግሞ ደስታ አገኝበታለሁ በሚል የሚጀምሩ / ሞዴል የሚሉትን ሰው በመመልከት አምነውበት የጀመሩ ናቸው።
- ክርስቲያን ከሆኑ ሰዎች 61 % የሚያህሉት እራስን በራስ በማርካት ልምምድ ውስጥ ተጠምደው ይገኛሉ።

ከዚህ መረጃ በመነሳት ከ61 % ሰዎች ይልቅ 41 % የሚሆኑት አለማድረጋቸውን በመመልከት እኛም ወደዚያው ምድብ መቀላቀል እንጂ "አብዛኛው ሰው የሚያደርገው ነው" በሚል የተሸነፈ አመለካከት ወደ 61 % እንዳንመደብ! ትክክል ያልሆነ ነገር ብዙ ሰው ስላደረገው ትክክል ሊሆን አይችልም። ሁሉም ሰው ቢያደርገውም ትክክል ሊሆን አይችልም።

ሴኩላርስ ምን ይላሉ?

እራስን በራስ ስለማርካት seculars የሚሉት በአብዛኛው ምንም አይነት ችግር የሌለበት ለደስታችን ሁል ጊዜ ልንፈፅመው የሚገባ ተግባር እንደሆነ ነው። በርግጥ ከጤና አንፃር ጉዳቶችን የሚጠቁሙም አሉ። ብዙ ጽሁፎች ለመመልከት ስሞክር ሀሳባቸው በፍፁም አንድ ክርስቲያን ሊኖረው ከሚችለው አስተሳሰብ የተለየ መሆኑን ነው

ያስተዋልኩት። ስለ ህይወት መዳን እንኳን እውነቱን ካልተረዳ ማንኛውም አይነት ሰው ጋር (የፈለገውን ያህል እውቀት ይኑረው) በአኗኗር ዘይቤ (Life style) ለመንፈሳዊ ህይወታችን መፅሐፍ ቅዱስን መሰረት ያደረገ ፅውቀት ይገኛል ብዬ አላስብም። ምክንያቱም መፅሐፍ ቅዱስ ሲናገር (1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ምዕ. 2) "መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም። #ለፍጥረታዊ_ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም።" እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ: እንዲህ ብሏል። " እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤" (ወደ ሮሜ ሰዎች 1:28) በእርግጥ አነሱ ስለሚሉት ብዙ ማለት እንችል ነበር ነገር ግን ትኩረት ማድረግ ወዳለብን አቅጣጫ በቀጣዩ ክፍላችን በክርስቲያኖች ዘንድስ ይሄ ተግባር ምን አይነት አመለካከቶች እንዳሉ እና መፅሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ የሚለንን ነገር እንመለከታለን።

መፅሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች

" ...እውነትም አርነት ያወጣችኋል..." ዮሐንስ 8:32 እውነትን ሳያውቁ አርነት መውጣት አይቻልምና አስቀድመን እውነቱን ማወቅ ይኖርብናል።

ወሲብን በተመለከተ ብዙ ርዕሰ ጉዳዮች መፅሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ቢነሱም እራስን በራስ ስለማርካት ግን በቀጥታ አልተነሳም። በቀጥታ መከልከሉን የሚናገር ወይም የሚነቅፍበት ክፍል የለም። አንዳንድ ክርስቲያኖች በቀጥታ ስላልተጠቀሰ በተግባሩ ላይ ወጥ የሆነ አቋም የላቸውም። ብዙ ክርስቲያኖች መፅሐፍ ቅዱስን መሰረት ያደረገ ቀጥተኛ መልስ መስጠት ያስቸገራቸው ጉዳይ ነው።

- በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዚህ ጉዳይ ጋር በአብዛኛው ተያይዞ የሚቀርበው የአውናን ታሪክ ነው።

" አውናንም ዘሩ ለእርሱ እንዳይሆን አወቀ፤ ወደ ወንድሙ ሚስት በገባ ጊዜ ለወንድሙ ዘር እንዳይሰጥ ዘሩን በምድር ያፈስሰው ነበር።" ዘፍ 38:9 በርግጥ እዚህ ጋር ያለው ሀሳብ ትኩረቱ እራስን በራስ ማርካት ነው?

" ይህም ሥራው በእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ ሆነበት፥ እርሱንም ደግሞ ቀሠፈው።" ዘፍ 38:10 እግዚአብሔርስ የቀሰፈው ለዚህ ነው? አይደለም! ነገር ግን አባቱ ይሁዳ በልጁ በዔር ምትክ ሚስቱን ትዕማርን አግብቶ ዘርን እንዲሰጥ ያዘዘውን ትዕዛዝ መፈፀም ባለመፈለጉ ክፋትን አስቦ ስላደረገው ተግባር ነው።

- ታዲያ እንዲህ ከሆነ እራስን በራስ ማርካት ትክክለኛ ተግባር ነው እያልን ነው? አይደለም!

መፅሐፍ ቅዱስ ሀጢአት ነው ወይም አይደለም በሎ ባልገለፀው ጉዳይ ላይ እኛ እራሳችን መወሰን አስቸጋሪ ቢሆንም በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዚህ ጋር ሊያያዙ የሚችሉ ጉዳዮችን በጥንቃቄ መመልከት እና መርህ (Principle) መያዝ ይኖርብናል።

ሲጀመር የግብረ ስጋ ግንኙነት (Sex) በንፅህና በባል እና በሚስት መካከል እንዲደረግ የራሱ የሆነ ዓላማ ኖሮት በእግዚአብሔር ነው የተፈጠረው። " መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን..." ዕብ 13:4 ስለዚህ እራስን በራስ ማርካት አግዚአብሔር በትዳር ውስጥ እንዲሆን የቀረፀውን (Design) ትክክለኛነት አለመቀበል ነው።

የወሲባዊ ውድቀት ሚጀምረው በሀሳብ ነው። ዋናው ሀሳቡ ነው። ሀሳባችንን ብቻ ነው ልናሸንፍ ምንችለው። ሀሳብን ካላሸነፍን ድርጊትን ማሸነፍ በፍፁም አንችልም። ጌታ ያለው ከውጫዊ ሀጢአት ነፃ እንድንሆን ብቻ ሳይሆን በልባችንም ለሀጢአት እንዳንገዛ ጭምር ነው። " እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።" ማቴ 5:28 [ለወንድ የተፃፈው ሴትንም ይወክላል።] እግዚአብሔር በተግባርም በሀሳባችንም ንፁህን መሆናችንን ነው የሚፈልገው። መፅሐፍ ቅዱስ መመኘትን , የራስን ፈቃድ ማስኬድን እንዲሁም ዝሙትን ይቃወማል። ስለዚህ ሰው እራሱን በራሱ ሲያረካ ምንም አይነት #ምኞት ወይም #ሀሳብ በአይምሮው የለም???? ስለዚህ በእርግጥም ልንቃወመው የሚገባን ተግባር ነው።

- ሌላው ሊነሳ የሚችለው ሀሳብ :- 'ሁለት ሰዎች ዝሙት ከሚሰሩ አንድ ሰው ብቻውን እራሱን በራሱ ቢያረካ የተሻለ ነው' የሚለው ሀሳብ ነው። በመሰረቱ የሀጢአት የተሻለ ያነሰ ሚባል ነገር የለውም። በአይምሮአችን ለየትኛውም አይነት ሀጢአት ልንገዛ አይገባም። ይሻላል ብለን ካሰብን ተገዛንለት ማለት ነው። በዮሐንስ ወንጌል 8:34 " ኢየሱስ መለሰ፥ እንዲህ ሲል። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባርያ ነው።" የሚለው የኢየሱስ ንግግር ይህንን ያሳየናል። የሀጢአት ባርያ ልንሆን አይገባም።

ከዚህ ተግባር መላቀቅ ስላቃተው አንድ ሰው የራሱን ክፍተት ለመሸፈን ሲል ትክክል ነው በማለት የፈለገውን ያህል ጥቅሶች ቢደረድር ትክክል ሊሆን አይችልም። ትክክል ያልሆነ ነገር ትክክል አይደለም!!

በነገር ሁሉ በንፅህና ልናድግ ይገባናል!!

ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተፅዕኖ

በመንፈሳዊ ህይወት

የሰው ልጅ በባህሪው ሀጢአትን ሲፈፅም አንድ #እውነት በውስጡ እየተዛባ ይመጣል። እሱም እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በምህረቱ ሊቀበለው እንደሚችል በውስጡ ያለውን መረዳት በማዛባት አዳም በገነት እያለ እንዳደረገው ከእግዚአብሔር መሸሸግ ወይም ከመንፈሳዊ ህብረቶች እና አገልግሎቶች እራስን ማግለልን ምርጫው ወደ ማድረግ ይመጣል። ዘፍ 3:9-10 እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ። ወዴት ነህ? አለው። እርሱም አለ። በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም። ይህ ሲሆን ደግሞ ሰይጣን ሁል ጊዜ በመክሰስ በመንፈሳዊ ህይወት ተስፋ ወደ መቁረጥ እንድንገባ ተግቶ በመስራት ከእግዚአብሔር ቤት እንድንርቅ ያደርገናል።

በስነ ልቦና

- በዚህ ልምምድ ውስጥ ያለ ሰው ትክክል እንዳልሆነ ሁል ጊዜ በንቃት የሚሰራው ህሊናው ስለሚነግረው አልፎ በመሄዱ መጨናነቅ (stress) ውስጥ ሊገባ ይችላል። ትክክለኛ የግብረስጋ ግንኙነትን ያሟላ ባለመሆኑ በዚህ ልምምድ ውስጥ ያለ ሰው በተፈጥሮ እውነት ከሆነው ዓለም እየራቀ ይመጣል። ከትክክለኛው የእርካታ መንገድ ውጪ የሆነን እርካታ በመለማመድ ትክክለኛውን አለመውደድን ያስከትላል። (አንዳንዱ ከልክ በላይ ሲለማመደው የህሊናው ምስክርነትም እየራቀው የተግባሩ አላስፈላጊነት ምንም ላይሰማው ወደሚችልበት ሁኔታ ያመራል። ይህ ደግሞ ከእውነቱ ክልል መውጣት ነው።)

- ድርጊቱ ሲደጋገም ማንነትን ወደ መቆጣጠር (ሱሰኝነት) ይሄዳል። የሁል ጊዜ ተገዢ ያደርጋል።

- እራስን በራስ ማርካት ችግሩ ልምድ ወይም ሱስ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከትላንት ይልቅ ተጨማሪ ርካታን ለማግኘት ሲባል የወሲብ ድርጊቶችን በሚያሳዩ ቪዲዮዎች ወይም ምስሎች (Pornography) መጠመድ እና ዘማዊነትን (ማመንዘርን) በመለማመድ ውስጥ መዝፈቁ ነው።

በትዳር

የፍቅር ግንኙነትን ከመረበሹም ባለፈ በትዳር ውስጥ የግብረስጋ ግንኙነት ከመደሰት ያለፈውን ትርጉም (ማለትም ፍቅርን መግለፅ, አንድነት, አንዱ ለአንዱ መሰጠት) ያበላሻል። ምክንያቱም ከትዳር በፊት በዚህ ልምምድ ውስጥ ያለፈ ሰው ትክክለኛውን (normal) የግብረስጋ ግንኙነት እርካታ ይተላለፈዋል። ከዛ ይልቅ እራስን በራስ ማርካት ምርጫው ወደመሆን የመጣበታል። ካገባ በኋላ በተደጋጋሚ በዚህ ልምምድ ውስጥ የሚያሳልፍ ባለትዳር ከትዳር አጋሩ ጋር ያለውን የወሲብ ፍላጎትም ይቀንሳል። ይህ ደግሞ በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ይረብሻል።

በጤና

እራስን በራስ የማርካት ድርጊትን በተደጋጋሚ የሚፈፅሙ ሰዎች በዋናነት የጀርባ ህመም እና ቶሎ ቶሎ መድከም እንደሚታይባቸው የጤና ባለሙያዎች ይገልጻሉ። እንዲሁም ድርጊቱ ሲበዛ ማንኛውም ትክክለኛ ተግባር በእለት ተዕለት

ኑሮአችን ያለልክ ሲደጋገም ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት እንዳለው ሁሉ እራስም በራስ ማርካትም ሲደጋገም የራሱ የሆኑ ተጨማሪ ችግሮች አሉት።

እስካሁን እየተነጋገርን ያለነው ሀሳብ በዚህ ልምምድ ውስጥ ያለን ሰው ሊረብሸው ይችላል። ፅሁፉ ማንም ሰው እንዲረበሽ የማድረግ ዓላማ የለውም። ነገር ግን ከዚህ ልምምድ መውጣት ይቻላል!

አዎ!! መላቀቅ ይቻላል።

እንዴት መላቀቅ ይቻላል?

"ብዙ ጊዜ ለማቆም ሞክሬያለሁ ግን አልቻልኩም!! ከዚህ ልምምድ ለመላቀቅ ምን ላድርግ?" በሚል የተደጋገመ ህይወት ውስጥ እያሳለፈ ላለ ሰው ሁሉ አንድ መፍትሔ አለ!

ከሁሉ በፊት ልብ ልንል የሚገባን ሁል ጊዜ ክርስቲያን በራሱ ብዙ ስለታገለ ከአንድ ልምምድ ሊላቀቅ አይችልም። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ ሰባት ከሀጢአት ጋር የነበረውን ግብግብ እንዴት እንዳሸነፈው በምዕራፍ 8 ላይ ይገልፃል። " የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም።" (ወደ ሮሜ ሰዎች 7:15) በማለት ከራሱ ጋር ሲታገል የነበረው... " በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና።" (ወደ ሮሜ ሰዎች 8:2) ሲል ነፃ መውጣቱን ይናገራል። ብዙ ውሳኔዎችን ለራሳችን ስላወጣን ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በመቅረብ በህይወት መንፈስ ህግ ልንመራ ያስፈልገናል። በእርግጥ መወሰናችን #ትክክል_ነው! ነገር ግን ውሳኔያችን አደንደመስታወት ስህተታችንን ሁል ጊዜ ያሳየናል እንጂ ከእኛ ላይ ስህተቱን ሊያስወግድልን አይችልም። ነገር ግን በፀጋው ቁጥጥር ስር ስንሆን ነው ማሸነፍ የምንችለው። አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር በቀረበ ልክ ከአላስፈላጊ ነገሮች እየራቀ መምጣቱ የሚዬታው ነው። ሁሉን የሚያስችለውን ፀጋውን ደግሞ በእምነት እንድንቀበል ተሰጥቶናል። ትልቁ መፍትሔ ይሄ ነው!!

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ተስፋ ወደመቁረጥ የሚመራ ድምፅ የሰይጣን ምክር ነው። ለመፀለይ ስትጀምር ሁል ጊዜ የሚከስህ ከሆነ ሁል ጊዜ በኢየሱስ ስራ ያገኘኸውን ማነንት (ከሀጢአት ባርነት ነፃ የወጣ ማንነት) በመንገር ማሸነፍ ትችላለህ። ጠላት የሚለው በሙሉ ውሸት ነው! እግዚአብሔር ከክርስቶስ ስራ የተነሳ ሁል ጊዜ በፍቅር እጆቹ ሊቀበለን ዝግጁ መሆኑን ልንዘነጋው አይገባም።

ምናልባት በአንድ ጊዜ ባይሆንም ሙሉ ለሙሉ ከዚህ ልምምድ ነፃ ለመውጣት ጊዜ ሊፈልግ ይችላል። የፈለገ ያህል ከፍተኛ ልምምድ ውስጥ ብትሆኑ እንኳን እግዚአብሔር ያለ ምንም ገደብ እንደሚወዳችሁ እና ሊያላቅቃችሁ እንደሚችል ልትዘነጉ አይገባም። " እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤" (ወደ ቲቶ 3:5)

በእርግጠኝነት ታሸንፋላችሁ በራሳችሁ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ሀይል!!

" የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ።" (1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 5:23) ስለዚህ ከዚህ በታች ያሉት ተጨማሪ ሀሳቦች እራሳችንን እራስን በራስ ከማርካት ልምምድ ነፃ መውጣት ለማስለመድ (Discipline) ልንጠቀማቸው እንችላለን።

1. በምክር እና በፀሎት ሊረዳኝ ይችላል ብለህ ወደምታስበው ክርስቲያን በመሄድ ማማከር እና እንዲፀልይልህ ማድረግ። " እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።" (የያዕቆብ መልእክት 5:16)

2. ወደዚህ ተግባር ከዚህ በፊት ከሚመሩህ ተግባሮች ሸሽ " ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ግን #ሽሽ፥ በንጹሕም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን እምነትን ፍቅርን ሰላምን አጥብቀህ ተከተል።" (2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:22) <u>ለምሳሌ:</u> pornography እንድናይ ፅድሎችን ከሚከፍቱ አካባቢዎች በመራቅ የመፅሐፍ ቅዱስ ርዕሰ ጉዳዮች በሚነጋገሩበት ህብረት መሳተፍ። ዋጋ ቢያስከፍልም አንዳንድ የምንወዳቸውን ነገሮች በመተው ከልምምዱ ነፃ መውጣት እንችላለን።

ይህ ፅሁፍ ለብዙዎች ነፃ መውጣት ምክንያት እንዲሆን እየተመኘው በ"sexuality" ዙሪያ የሚያገለግሉ Betty Miller የተባሉ አንድ እናት በፅሑፍ የፀለዩትን ፀሎት በማስከተል ፅሁፌን ላጠቅቅ።

“Father, we thank you for bringing this person into our website (Channel). We lift them up to you now and let them know your cleansing love and power. We thank you that he whom the Son has set free, is free indeed. We speak this freedom into the life of this one whom the devil has bound in shame. We speak healing and deliverance and we break every tie that has kept them under a spirit of addiction and perversion. We stand against the Evil One and his every plan to bring destruction in this one’s life. Father, in faith, and by the power and authority You have given us, we declare that this one is FREE in the name of Jesus! We commit them to Your care. We ask these things in the precious name of Your son, Jesus Christ.”

በትዕግስት ስላነበባችሁ ጌታ ይባርካችሁ።

ፅሁፉን የተለያዩ ምንጮችን በመጠቀም ያዘጋጀሁት ተካልኝ ደምሴ ነኝ።

በቴሌግራም ቻናል @sexualpurity ላየረ የቀረበ።